# በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች

በሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች የስራ ቡድን የቀረበ

ህዳር 2015 ዓ.ም

የሽግግር ፍትህ
TRANSITIONAL JUSTICE

# የገለጻው ይዘት

1. በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ አስፈላጊነት
2. የሽግግር ፍትሕ አላባዎች/ስልቶች
   - ሀ. ክስ
   - ለ. ማፈላለግና ይፋ ማውጣት
   - ሐ. እርቅ
   - መ. ምህረት
   - ሠ. ማካካሻ
   - ረ. ተቋማዊ ማሻሻያ
3. ሌሎች ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች

1

# በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ አስፈላጊነት

**አስፈላጊነት?**

- ሀገራዊ አውዱ የተሟላ የሽግግር ፍትህ ተፈፃሚነትን የሚሻ መሆኑ
- ለሀገረ መንግስቱ ግንባታ እና ቀጣይነት ያለው ፋይዳ
- ለዲሞክራሲ ሽግግርም ሆነ ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ ያለው ሚና
- ለሰብአዊ መብቶች መከበር እና ለህግ የበላይነት መረጋገጥ

2

ሀ.

# የሽግግር ፍትሕ አላባዎች/ስልቶች

## ክስ: የትኛዎቹ ጉዳዮች ያስከስሳሉ?

**አማራጭ አንድ:-**

**ጉልህ የሆኑ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ውይም ከባድ ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ማከናወን**

**ጠንካራ ጎኖች**

- ሌሎች የሽግግር ፍትህ ስልቶችም ተግባራዊ እንዲደረጉ እድል ይሰጣል ፤
- የተፋጠነ እና የተቀላጠፈ የፍትህ ሂደት እንዲኖር ያስችላል፣
- የበደሎቹን ግዝፈትና አይነት በሚያሳይ መልኩ እንዲከናወን አስተዋፅዎ ያደርጋል፣
- ሀገራት የተጣልባቸዉን የመክሰስ ግዴታቸዉን መወጣት በመሆኑ ፣

**ሥጋቶች፡**

- በትክክል ምርመራ በማካሄድ ማስረጃ የማግኘት ችግር ሊያጋጥም ይችላል፣
- የድርጊቱን ስፋት፣ ምንነትና ግዝፈት በተሟላ መልኩ አያሳይም፤
- እነዚህን ወንጀሎች ሊቀጣ የሚችል የህግ ማዕቀፍ ክፍተት፡፡

# የትኛዎቹ ጉዳዮች ያስከስሳሉ?

**አማራጭ ሁለት፡**

**ሁሉንም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ያካተተ የክስ ሂደት ማከናወን።**

**ጠንካራ ጎኖች፡**

- በሁሉም አጥፊዎች ላይ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ ያደርጋል፣
- የተበዳዮችን የፍትህ ፍላጎት በተሻለ መልኩ ሊያረካ ይችላል፣
- በጥሰቶች መካከል ማበላለጥ እንዳይኖር እና በድጋሜ ወንጀሎቹ እንዳይፈፀሙ

**ሥጋቶች፡**

- ሌሎች የሽግግር ፍትህ ስልቶችም ተግባራዊ እንዳይደረጉ ያደርጋል
- ምህረትን እንደ ሽገግር ፍትህ ስልት ተግባራዊ ለማድረግ እድሉ አጥቦ እውነትን የማውጣት ስራውን ከባድ ያደርገዋል
- የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊሸከም ከሚችለው በላይ ሊሆን ይችላል፤
- የፍርድ ቤቶችን የስራ ጫና ሸክም የሚጨምር እና ከፍተኛ የሆነ ሀብት የሚጠይቅ መሆኑ
- ከጉዳዮቹ ስፋት አንፃር በአጭር ጊዜ እልባት መስጠት የማይቻል በመሆኑ በሂደቱ የመሰላቸት እና ያለመርካት ስጋት።

# በየትኛዎቹ አጥፊዎች ላይ ክስ ይመሰረታል?

**አማራጭ አንድ፡**

**ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ** (most responsible)

**ጠንካራ ጎኖች፡**

- የምርመራ እና የክስ ስራ የሚሰሩ አካላት ላይ ከፍተኛ የስራ ጫና እንዳይኖር ያግዛል፣
- በድርጊቱ ዋና ተዋንያን ያልሆኑ ሰዎችን አስመልክቶ ሌሎች የሽግግር ፍትህ አማራጮች እንዲተገበሩ፣
- የፍርድ ቤቶችን የስራ ጫና በመቀነስ የሀገሪቱ ውስን ሀብት ለከባድ ጥሰት ፈፃሚዎች እንዲውል፣
- ያለልዩነት ከፍተኛ ተጠርጣሪዎችን በመክሰስ ሽግግሩን በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይረዳል፤

**ሥጋቶች፡**

- በግል ተበዳዮችና በማህበረሰቡ ዘንድ ቅሬታን ሊፈጥር ይችላል፣
- አንዳንድ ጥፋት ፈፃሚዎች በድጋሚ ወንጀል እንዲፈፅሙ ሊያበረታታ ይችላል፣
- አሰራሩ ለአድሎ እና  ተገቢ ላልሆነ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፣

# በየትኛዎቹ አጥፊዎች ላይ ክስ ይመሰረታል?

**አማራጭ ሁለት፡-**

**የወንጀል ክስ ሂደቱ በማንኛውም ደረጃ በጉልህ ሰብአዊ መብት ጥሰቶች ወንጀሎች ውስጥ የተሳተፉ ሰዎችን በማካተት የሚከናወንበት አማራጭ**

**ጠንካራ ጎኖች፡**

- በሂደቱ ቅሬታዎች እንዳይነሱ ያደርጋል፣
- በደል የደረሰባቸው ሰዎች የፍትህ ፍላጎት በተሻለ መልኩ እንዲሟላ እድል ይሰጣል፣

**ሥጋቶች፡**

- ከክስ ውጪ ላሉ የሽግግር ፍትህ ስልቶች ትኩረት እንዳይሰጥ ያደርጋል፣
- ከብዛቱ የተነሳ
    - የሽግግር ሂደቱ ክስ ሂደት ሊሸከም ከሚችለው በላይ እንዳይሆን ያሰጋል፣
    - የፍትህ መዛባት ሊያስከትል መቻሉ፣

## ተቋማዊ ጉዳዮች ክስ ላይ

### 1. ፍርድ ቤቶችን በሚመለከት

**አማራጭ አንድ፡-**

**በከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውስጥ ልዩ ችሎት በማቋቋም ክሶቹን በመስማት ውሳኔ መስጠት**

**ጠንካራ ጎኖች**

- ባሉ ተቋማት ውስጥ ተግባራቱ እንዲከናወኑ ስለሚያደርግ ሀብት ይቆጥባል፤
- ያለውን የሰው እና የተቋም አቅም ለመጠቀም ያስችላል፤
- በፍርድ ቤቶቻችን ገለልተኝነት እና አቅም ላይ ያለውን ጥያቄ ለመመለስ የተሻለ ነፃነት ያለው አወቃቀርና ተገቢ ማጣራት በማድረግ ዳኞችን በመመደብ በቀጣይ ፍርድ ቤቶች ለሚያደርጉት የለውጥ ስራ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

**ሥጋቶች**

- በቂ የሆነ ለዉጥ ባልተደረግባቸው ወይም ተደርጎባቸዋል ተብለዉ በማይታሰቡ የፍርድ ቤት ችሎቶች በመጠቀም እነዚህን ክሶች ማካሄድ በሂደቱ እና በውጤቱ ላይ የተአማኒነት እና የቅቡልነት ጥያቄ ያስነሳል፤
- አሁን ባለው ሁኔታ ከክሶቹ ውስብስብነት እና ግዝፈት አንፃር የአቅም ውሱንነት ሊኖር ይችላል።

# ፍርድ ቤቶችን በሚመለከት

**አማራጭ ሁለት፡-**

**ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም ክሶቹን በመስማት ውሳኔ መስጠት**

**ጠንካራ ጎኖች**

- አዲስ ተቋም እና አደረጃጀት በመፍጠር የተሻለ ቅቡልነት እና ገለልተኝነት ያለው ተቋም እንዲኖር እድል ይፈጥራል፤
- የወንጀሎቹን ውስብስብነት የሚመጥን አቅም ያላቸውን ዳኞች ለመመደብ እና በተሻለ ብቃት ክሶቹን ለማስተናገድ ያስችላል፡፡

***ሥጋቶች፡***

- ልዩ ችሎቶችን ከመሰየም አንፃር ህገመንግስታዊ ጥያቄዎች ሊነሱበት ይችላል፤
- አዲስ ተቋም የማቋቋም የሰው ሀይል እና አስፈላጊ ግብአቶችን የማሟላት እና መሰል ተግባራትን ለማከናወን ጊዜ የሚወስድ መሆኑ፤
- ዘላቂነት ላለው ተቋም ግንባታ ያለው አስተዋፅዎ አነስተኛ ነው፡፡

# ምርመራ እና ክስን በሚመለከት

**አማራጭ አንድ፡**

**ባለው የፖሊስ እና የዐቃቤ ህግ ስር የተለየ ቡድን መመስረት**

## ጠንካራ ጎን

- ባሉ ተቋማት ውስጥ ተግባራቱ እንዲከናወኑ ስለሚያደርግ ሀብት ይቆጥባል፣
- ያለውን የሰው እና የተቋም አቅም ለመጠቀም ያስችላል፣
- እንዲህ አይነት ስራዎችን የመስራት ልምድ ቀጣይነት እንዲኖር በማድረግ ለተቋም ግንባታ አስተዋፅዎ ያደርጋል፣

## ሥጋቶች

- በቂ የሆነ ለዉጥ ባልተደረግባቸው፤ ወይም ተደርጎባቸዋል ተብለዉ በማይታሰቡ የፍትህ ተቋማትን በመጠቀም፤ እነዚህን ክሶች ማካሄድ በሂደቱ እና በውጤቱ ላይ የተአማኒነት እና የቅቡልነት ጥያቄ ያስነሳል፣

# ምርመራ እና ክስን በሚመለከት

**አማራጭ ሁለት፡**

አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጪ ሌላ ምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር ልዩ የዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን መመደብ

**ጠንካራ ጎን**

- የተሻለ ቅቡልነት እና ገለልተኝነት ያለው ተቋም እንዲኖር እድል ይፈጥራል፣
- የምርመራ እና የክስ ስራው በአንድ ተቋም የሚሰራ በመሆኑ / ፍጥነት፣
- ለተቋሙ ልዩ ትኩረት / አስፈላጊውን ድጋፍ ለማግኘት / የተሻለ አቅም ፣
- ከተቋሙ ጋር በትብብር እንዲሰሩ ያበረታታቸዋል፣
- የተሻለ ባለቤትነት እና ተጠያቂነት ይፈጥራል

**ሥጋቶች**

- የሰው ሀይል እና አስፈላጊ ግብአቶችን የማሟላት ጊዜ የሚወስድ መሆኑ፣
- በምርመራም ሆነ በክስ ስራ አሁን ካሉት ተቋማት ውጪ ያሉ ብቃት እና ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ለማግኘት አለመቻል
- ዘላቂነት ላለው ተቋም ግንባታ ያለው አስተዋፅዎ አነስተኛ ነው፣
- መንግስት ለዚህ ተቋም አስፈላጊ ነገሮችን  የማሟላት ኃላፊነት ስለሚኖርበት ውስን የሀገር ሀብት  ላይ ጫና መፍጠሩ፣

## እውነትን ማፈላለግና ይፋ ማውጣት?

እውነትን በማጣራት ሂደት ዋና ዋና ተግባራት ምንድን ናቸው?

**እውነትን በማጣራት ሂደት ዋና ዋና ተግባራት ምንድን ናቸው?**

- የተጎጂዎችን ተሳትፎ ማረጋገጥ፡
- ጥፋት ፈፃሚዎችን ማሳተፍ፡
- በደሎችን መሰነድ፡
- የተጣራውን እውነት ለማህበረሰቡ ማሳወቅ፡ በእውነትን ማጣራት ሂደት በደሎችን መሰነድ ብቻ ሳይሆን የተጣራውን እውነት ለማህበረሰቡ ማሳወቅ እና ለተጎጂዎችን ሰቆቃ ሕዝባዊ እውቅና መስጠት መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

# እውነትን ማፈላለግና ይፋ ማውጣት ሂደቱን ማን ያከናውነዋል?

**አማራጭ አንድ፡**

አዲስ በሚቋቋም የሀቅ፤ የፍትህ እና የእርቅ ኮሚሽን አማካኝነት

**ጠንካራ ጎኖች**

- በሽግግር ፍትህ ሂደቶች ኮሚሽን ማቋቋም አለምአቀፍ ተቀባይነት ያለው እና የተለመደ አካሄድ ነው፤ ይበልጥም ውጤታማ ያደርገዋል፣
- ካላቸው ነጻነትና ገለልተኛነት እና በሂደታቸውም ማህበረሰቡን የሚያሳተፉ በመሆኑ ተአማኒነቱ አላቸው
- በዘርፉ ታዋቂ የሆኑ ባለሙያዎች እና አመራሮችን የተቋሙ አካል በማድረግ ስራው በእውቀት እንዲመራ ያስችላል።
- እውነት በቅድመ ሁኔታ ላይ ለሚሰጥ ምህረት ቅድመ ሁኔታ በመሆኑ፣ የበዳዮችን እና የተጎጂዎችን ተሰሚነት እና ተሳትፎ ማረጋገጥ፣ ማጣራት፣ መሰነድ እና ይፋ ማድረግን ሚጠይቅ፣ መጠነ ሰፊ መድረኮችን እና ቃል መቀበያ መንገዶችን መዘርጋት የሚያስፈልገው ሰፊ ስራ በመሆኑ ይህንን በተግባር በመፈጸም አላማ በተቋቋመ ኮሚሽን መከናወኑ ይበልጥ ተገቢ ነው፣

**ስጋቶች**

- በሀገር ካለው ውስን ሀብት አንፃር ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ነው
- ኮሚሽን በማቋቋም ተግባራቱን ማከናወን ተሞክሮ ያልተሳካ አካሄድ በመሆኑ በድጋሚ ይህንን ተቋም ለማቋቋም የሚኖረው እድል ዝቅተኛ መሆኑ፤

# እውነትን ማፈላለግና ይፋ ማውጣት ሂደቱን ማን ያከናውነዋል?

**አማራጭ ሁለት፡-**

በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ወይም በቅርቡ በተቋቋመው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት እውነት የማጣራቱን ተግባር ማከናወን

**ጠንካራ ጎኖች**

- አሁን ባሉ ተቋማት በመጠቀም በሀገር ያለውን ውስን ሀብት ይቆጥባል፤
- ተቋማዊ አቅምን ይገነባል፡፡

**ስጋቶች**

- ባለባቸው ከፍተኛ ሀላፊነት የተነሳ እውነትን የማጣራት ሰፊ ስራ በውጤታማነት ላያከናውኑት ይችላሉ፤
- በተለይም ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ብሄራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ከመሆኑ አንፃር የቁጥጥር እና የክትትል ተግባራቱ ላይ ተጽእኖ ያሳድርበታል፤ አለምአቀፍ ተሞክሮውም እንደሚያሳየው እንደዚህ አይነት ተቋማት በሂደቱ ቀጥተኛ ፈፃሚዎች እንዲሆኑ አይመከርም፤
- በሽግግር ፍትህ ሂደቱ እውነትን ለማጣራት ማከናወን የሚያስፈልገውን ውስብስብ ተግባር እና መከተል ያለበትን አሳታፊ ሂደት ተከትሎ ለመስራት የሚያስችል አቅም የላቸውም፤
- ከተቋማቱ ውጪ ያሉ በዘርፉ እውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች እና አመራሮችን በሂደቱ ለመጠቀም እድል አይሰጥም፡፡

ሐ

# እርቅ

እርቅ

*በሽግግር ፍትህ አውድ ውስጥ እርቅ አንድ ሂደት ወይም በራሱ ግብ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።*

**የእርቅ ደረጃዎች**

- ግላዊ እርቅ፡-
- የግለሰቦች እርቅ፡-
- ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እርቅ፡-
- ተቋማዊ እርቅ፡-

## የእርቅ ሂደቱን ማን ያከናውነው?

**ጠንካራ ጎኖች**

- በሽግግር ፍትህ ሂደቱ እርቅ አንደኛው ግብ እንደመሆኑ በዚህ ሂደት ተግባራቱን ለመፈጸም በተቋቋመ አካል መከናወኑ ይበልጥ ውጤታማ ያደርገዋል፣
- እነዚህ ተቋማት ካላቸው ነጻነትና ገለልተኛነት እና በሂደታቸውም ማህበረሰቡን የሚያሳተፉ በመሆኑ ተአማኒነቱ/ ቅቡልነቱ ከፍ ያለ ይሆናል፣
- በዘርፉ ታዋቂ የሆኑ ባለሙያዎች እና አመራሮችን የተቋሙ አካል በማድረግ ስራው በእውቀት እንዲመራ ያስችላል፡፡

**ስጋቶች**

- በሀገር ካለው ውስን ሀብት አንፃር ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ነው
- ኮሚሽን በማቋቋም ተግባራቱን ማከናወን ተሞክሮ ያልተሳካ አካሄድ በመሆኑ በድጋሚ ይህን ተቋም ለማቋቋም የሚኖረው እድል ዝቅተኛ መሆኑ

**አማራጭ አንድ፡**

**የሀቅ፤ የፍትህ እና የእርቅ ኮሚሽን አማካኝነት፡**

# የእርቅ ሂደቱን ማን ያከናውነው?

**አማርጭ ሁለት:-**

**በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት የእርቅ ተግባራቱን ማከናወን፡**

**ጠንካራ ጎኖች**

- አሁን ባሉ ተቋማት በመጠቀም በሀገር ያለውን ውስን ሀብት ይቆጥባል፣
- ከገለልተኝነት እና ነፃነት አንፃር የተሻለ ተቀባይነት ይኖረዋል፣

**ስጋቶች**

- ኮሚሽኑ ከፍተኛ ሀላፊነት እና መጠነ ሰፊ ተግባራት የተሰጠው በመሆኑ የእርቅን ተግባራት በውጤታማነት ለማከናወን ይቸገራል፣
- አሁን ያለው የኮሚሽኑ ስልጣን ይህን የማያካተት በመሆኑ የህግ ማሻሻያ ያስፈልጋል፣ ይህም ጊዜ ይወስዳል፣ አሰራሩም የምክክር ኮሚሽኖች ለየት ያለ ስልጣን የሚሰጠው በመሆኑ በሞዴል ደረጃ ከአለማቀፍ ልምዶች ጋር የተጣጣመ ያለመሆን ችግር ሊኖር ይችላል፣
- በሽግግር ፍትህ ሂደቱ እርቅን ከሌሎች ሂደቶች ጋር አቀናጅቶ መተግበር ላይ ክፍተት ሊፈጠር ይችላል፣

መ

# **ምህረት** ፡- ስለምህረት ቅድመ-ሁኔታዎች?

**የምህረት መስፈርት?**

ምህረት የሚሰጠው የምህረት ቅደመሁኔታን ላሟላ ነው፡፡

- የአጥፊዎች ተሳትፎ መጠን
- የወንጀሉ ይዘት እና ክብደት
- እውነትን ማውጣት
- መፀፀት እና ይቅርታ መጠየቅ
- መተባበር
- ህገ መንግስት አንቀጽ 28

# ምህረት የመስጠቱን ሂደት ማን ያከናውነዋል?

**አማራጭ አንድ፡**

**በእውነት እና እርቅ ኮሚሽን አማካኝነት መስጠት፡**

**ጠንካራ ጎኖች**

- የምህረቱ አላማ እውነትና ማውጣትና እርቅን ማስፈን እንደመሆኑ ለዚህ ሂደት በተቋቋመ አካል መሰጠቱ ይበልጥ ውጤታማ ያደርገዋል፣
- በዘርፉ ታዋቂ የሆኑ ባለሙያዎች እና አመራሮችን የተቋሙ አካል በማድረግ ስራው በእውቀት እንዲመራ ያስችላል፡፡
- እነዚህ ተቋማት ካላቸው ነጻነትና ገለልተኛነት እና በሂደታቸውም ማህበረሰቡን የሚያሳተፉ በመሆኑ ማህበረሰቡን ያመነበት ወደ ዘላቂ ሰለም የሚሸጋገር ምሀረት እንዲሰጥ ያደርጋል
- አጥፊዎችን እምነት ኖሯቸው በሂደቱ እንዲሳተፉ በማስቻል የሽግግር ስርአቱን ቀልጣፋ ያደርገዋል
- ምህረት ከተሰጠ በኋላ መመዘኛዎች የሚላታቸውንና ምህረቱ ቀጣይነት ለማረጋገጥ ምቹ በመሆኑ

**ስጋቶች**

- በሀገር ካለው ውስን ሀብት አንፃር ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ነው
- ኮሚሽን በማቋቋም ተግባራቱን ማከናወን ተሞክሮ ያልተሳካ አካሄድ  በመሆኑ በድጋሚ ይህንን ተቋም ለማቋቋም የሚኖረው እድል ዝቅተኛ መሆኑ
- ከሀገሪቱ የቆዳ ስፋት፣ ከሂደቱ ስፋት አንፃር እና ኮሚሽኑ ከሚኖረው የተወሰነ የጊዜ ገደብ አንፃር የተደራሽነት ችግር ሊኖር ይችላል

# ምህረት የመስጠቱን ሂደት ማን ያከናውነዋል?

**አማራጭ ሁለት፡**

አሁን ባለው የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀትን በማሻሻልና ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በመጠቀም ምህረትን መስጠት፡

**ጠንካራ ጎኖች**

- በሀገር ያለውን ውስን ሀብት ይቆጥባል
- ተቋማዊ አቅምን ይገነባል

**ስጋቶች**

- አሰራሩ በሽግግር ፍትህ መንፈስ የተቀረፀ ባለመሆኑ ውጤታማነቱ አጠራጣሪ ነው፣
- በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ምህረት አሰጣጥ የሚኖረውን ውስብስብ ተግባራት ለመስራት የሚያስችል አደረጃጀት አይደለም፣
- ተአማኒነቱ እና ቅቡልነቱ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው፣
- አጥፊዎችን እምነት ኖሯቸው በሂደቱ እንዲሳተፉ አያስችልም

ሠ

# ማካካሻ

ማካካሻ

**ምን አይነት የማካካሻ አይነቶች ሊተገበሩ ይችላሉ**

- ወደነበረበት መመለስ፡
- ካሳ፡
- እርካታ/ፈውስ፡
- ማገገም፡
- የጋራ ካሳ፡
- መታሰቢያ፡

**ዋና ዋና ተግባራት**

- የማካካሻ ስርአቱን በሚመለከት የህግ ማእቀፍ እንዲኖረው ማድረግ፡
- በግል ካሳ የሚሰጣቸውን ተበዳዮች መለየት፡
- በማካካሻ ስርአቱ ጥፋት ፈፃሚዎችን ሀላፊነት የሚወስዱበት መንገድ መለየት፡
- የተጎጂዎች ፈንድ ማቋቋም፡

# የማካካሻ ስርአቱን ማን ይመራዋል/ ያስተባብረዋል?

**አማራጭ አንድ፡**

**በእውነት እና እርቅ ኮሚሽን**

**ጠንካራ ጎኖች**

- ለተጎጂዎች ማካካሻ የመስጠቱ ሂደት ለተጎጂዎች ተፈጻሚ የሚሆን ውጤታማ የማካካሻ መርሀ ግብር መቅረጽ ውስብስብና ሰፊ እቅድ እና ማስተባበርን የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ራሱን የቻለ ኮሚሽን በማቋቋም ተግባራዊ ማድረግ ስራው የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል፣
- ኮሚሽኑ ሌሎች ተግባራቶቹን ሲያከናውን የተጎጂዎችን እና አጥፊዎችን ማንነት እና ሁኔታ ተለይቶና ተመዝግቦ የሚያዝ በመሆኑ ይህ መረጃ ማካካሻው የሚሰጣቸውን/ሊሰጣቸው የሚገባ ተጎጂዎች እና ሊሰጥ የሚገባውን ማካካሻ አይነትና መጠን፣ አጥፊዎችንም ተሳትፎ መጠን ለመወሰን ስለሚያስችለው የበለጠ ውጤታማ ያደርገዋል፣
- እነዚህ ተቋማት ካላቸው ነጻነትና ገለልተኛነት እና በሂደታቸውም ማህበረሰቡን የሚያሳተፉ በመሆኑ ተአማኒነቱ ከፍ ያለ ይሆናል፣

**ስጋቶች**

- በሀገር ካለው ውስን ሀብት አንፃር ኮሚሽን ማቋቋም ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ነው
- ኮሚሽን በማቋቋም ተግባራቱን ማከናወን ተሞክሮ ያልተሰካ አካሄድ በመሆኑ በድጋሚ ይህንን ተቋም ለማቋቋም የሚኖረው እድል ዝቅተኛ መሆኑ፣
- የተደራሽነት ችግር ሊኖር ይችላል፣
- ማካካሻ በራሱ የሚፈልገው ብቃት እና አቅም (ለምሳሌ የካሳ መጠንን መወሰን) የተለየ በመሆኑ ኮሚሽኑ ተግባራቱን ለማከናወን የሚስችለው ቁመና ላይኖረው ይችላል፤
- የካሳ ጉዳይ በሀገራችን ካለው አስፈላጊነት አንፃር በጊዜ ለተገደበ ኮሚሽን ስልጣኑን መስጠት ቀጣይነት እንዳኖረው ያደርጋል፣

# የማካካሻ ስርአቱን ማን ይመራዋል/ ያስተባብረዋል?

**አማራጭ ሁለት፡**

የግል ካሳን ጉዳይ በመደበኛው የህግ ሰርአት በፍርድ ቤቶች እንዲታይ በመተው፤ የጋራ ማካካሻ ጉዳዮች ላይ ተገቢውን የህግ ማሻሻያ በማድረግ በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ወይም በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት የማካካሻ ስርአቱን የማስፈፀሙን ተግባራትን ማከናወንን ይተልማል።

**ጠንካራ ጎኖች**

- አሁን ባሉ ተቋማት በመጠቀም በሀገር ያለውን ውስን ሀብት ይቆጥባል፣
- ተቋማዊ አቅምን ይገነባል፣ ቀጣይነት እንዲኖር ያስችላል
- በፍትሀብሄር ህጉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በፈፀሙ ግልሰቦች የግል ተጠያቂነትን እንዲኖር በማድረግ ግለሰባዊ ሀላፊነትን ይበልጥ ያረጋግጣል፤

**ስጋቶች**

- ተቋማቱ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የማካካሻ ስርአቱን ለመተግበር የሚያስፈልገውን ውስብስብ ተግባራት እና መከተል ያለበትን አሳታፊ ሂደት ተከትሎ ለመስራት የሚያስችል አቅም የላቸውም፣
- በሽግግር ፍትህ ስርአቱ ተግባር ላይ ከሚውሉ ሌሎች መንገዶች ጋር የማካካሻ ስርአቱን ለማቀናጀት አስቸጋሪ ያደርገዋል፣
- በመደበኛው የህግ ስርአት የተጎጂዎች ማካካሻ የማግኘት መብትን ማስፈፀም በመደበኛ ጊዜያትም ጭምር አዳጋች በመሆኑ ውጤታማ ላይሆን ይችላል፤
- ሁለቱም ተቋማት ከፍተኛ ሀላፊነት እና መጠነ ሰፊ ተግባራት ያላቸው በመሆኑ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ማካካሻ ስርአት ሊኖረው ከሚችለው ከፍተኛ ስራ ጫና አንጻር በውጤታማነት ላያከናውኑት ይችላሉ፣
- ሁሉም ጉዳዮች በፍርድ ቤት ስርአት ላያልፉ ስለሚችሉ በተጎጂዎች መካከል ልዩነት እንዲኖር ያደርጋል፤

## ተቋማዊ ማሻሻያ

## በሽግግር ፍትህ ሂደቶች የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት ምን ምን ሊያካትቱ ይችላሉ?

ተቋም ማሻሻያ?

- መለየት እና ማጥራት
- ከስራ እና ከሀላፊነት ማግለል
- የህግ እና የአሰራር ለውጥ

# የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራቱ በማን ይከናወናሉ?

**አማራጭ አንድ፡**

**የተቋማትን ለውጥ የሚያስተገብር የልየታ፣ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ስልጣን የተሰጠው ገለልተኛና ነጻ የሆነ አካል በማቋቋም ተግባራቶቹን ማከናወን፡**

## ጠንካራ ጎኖች

- የማጥራት ሂደቱ በነፃነት እና በገለልተኝነት የመከናወን እድሉን ያሰፋዋል- በመሆኑም ቅቡልነቱን ይጨምራል፣
- ፖለቲካዊ እና ኢመደበኛ የሆኑ የጎሳ እና የብሄር ቡድኖች ጣልቃ ገብነትን ለመከላከል ያስችላል፣
- ከሌሎች ሽግግር ፍትህ ሂደት መንገዶች ጋር ለውን መስተጋበር የበለጠ ጠንካራ ያደርገዋል፣

## ስጋቶች

- በሀገር ካለው ውስን ሀብት አንፃር ሌላ አካል ማቋቋም ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ነው፣
- በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ የልታ እና የማጣራት ተግባራት በስኬት ለማከናወን የሚስችል ፖለቲካዊ ቁመና ላይኖረው ይችላል፣

# የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራቱ በማን ይከናወናሉ?

**አማራጭ ሁለት፡**

**በሁሉም ተቋማት ውስጥ የልየታ፣ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ሀላፊነት ያላቸው ቡድኖች በማዋቀር ተግባራቶቹን ማከናወን**

## ጠንካራ ጎኖች

- አሁን ባሉ ተቋማት ውስጥ ሂደቱ እንዲከናወን በማድረግ በሀገር ያለውን ውስን ሀብት ይቆጥባል፣
- ተቋማዊ አቅምን ይገነባል፣ ቀጣይነት እንዲኖር ያስችለዋል፣
- በተቋማቱ ባለቤትነት እንዲመራ፣ ተገቢ የፖለቲካ ቁመና እንዲኖረው እና ሊመጡ የሚችሉ ስጋቶችን በቅርበት በማወቅ መፍትሄ ለመስጠት ያመቻል፣

## ስጋቶች

- ሂደቱ በነፃነት እና በገልልተኝነት የመከናወን እድሉን ያጠበዋል፣ የቅቡልነት ተግዳሮቶች ይፈጥራሉ፣
- በሽግግር ፍትህ ሂደት ወቅት በሚፈለገው መጠን አለማቀፋዊ መስፈርቶች በመጠቀም የማከናወን አቅም እና ፍልጎት ላይኖር ይችላል፤
- ከእውነተኛ ማጥራት እና ማግለል ይልቅ ክፍተት እና ግጭት እንዳይፈጠር በመስጋት ፖለቲካዊ ጉዳዮችን መሰረት ያደረጉ ውሳኔዎች የመኖር እድላቸው ይጨምራል፣

# ውሳኔ የሚስፈልጋቸው ሌሎች ጉዳዮች

❖ **የጊዜ ገደብ**

**የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር?**

**አማራጭ አንድ፡**

ከ1983 በፊት ባሉ ጊዜያት

**አማራጭ ሁለት፡** 1983 ጀምሮ

**አማራጭ ሶስት፡**

ከ1987 ጀምሮ

**አማራጭ አራት፡**

ከ2010 ጀምሮ

**አማራጭ አምስት፡**

ለክስ ጉዳይ 1987 ጀምሮ፣ ለእርቅና ማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ እና መስረጃ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ

## ❖ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ክልሎች/ የከተማ መስተዳደሮች እና የባህላዊ የፍትህ ሥርአቶች ሚና

**ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች**

- በፌደራል መንግስቱ በሚካሄዱ  የሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ ክልሎች ጉልህ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል።
- እውነትን በማፈላለግ፣ የምህረት እና የእርቅ ሂደቶች ውስጥ መደበኛ ፍትህ ስርአቱን ከባህላዊ ስርአት ጋር በማቀናጀት ሰብዓዊ መብቶችን ባከበረ መልኩ ይፈፀማል
- የባህላዊ  ፍትህ ስርዓት በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ የሚሳተፉ ተቋማትን ጫና በመቀነስ ብቻ ሳይሆንበ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ዘላቂ ሰላም፣ ፍትህ እና እርቅ በማምጣት ስኬታማ እንዲሆን አስተዋፅዎ ያደርጋል።

እናመሰግናለን!